## ወጣቱ

ኀሀ በማለዳ

በፀሐይ ተሞልታ

ጀንበር በጨረቃ

ስትታይ ኀርምታ

ውበቱአም ምናኔ

ድምቀቱአም የዋይታ

ፋካቱአም የሃዘን

የእንጉርጉሮ ፈሽታ

ሆኖ ቢታየው ነው

ንቀ ቢኀፈየው

እምቢኝ ለነጻነት

ብሎ የረገፈው

ያ የወጣት ተምሳሌ

የነገ ፈንጣቂ

ተስፋ ያላጉጉው

ለአባት አደራ ወግ እንጂ

ምንዳ አሜኬላ ያልሆነ ናፋቂ።

***ቀንጅትን ብለው ለኢትዮጵያዊነት በወያኔ ወታደሮች በግፍ ለተሰው ወጣቶች***

***ሥዩም ደገፋ ጥቅምት 2000 ዓ.ም***

* * * * * *

## ድቅድቁ ጨለማ

የእምነት የቃልኪዳን

የደም ያደራ ቃል

ገብቶት ላላጤነው

ማንስ እውነት ያውቃል?

ለዚህ ያደራ ቃል

የፀና በምነቱ

ጥናት የጉልበቱ

ምርኩዝ አንደበቱ

ብርታት ጥንካሬው

ህልው እሱነቱ
ኃይሉ የመከታው
እጥንት ወ - ጉልጥምቱ!
በረሃብ በጠኔ
ተነሱ ሊቀጡት
በመከራው ፌዝ
በስቃዩ ሃፎት
ከጀሉ ተመኙ
ሊከቱበት ሃኬት
ደዌ ቢያሸንፈው
መራመድ ተስኖት
አላላውስ ቢለው
እምቢኝ ነው ያለው
ለዚያ ያደራ ቃል
ማተብ የቁጠረው።
ተስፋችን እንዲመክን
እንዲቀርብን መና
እያደር ፅልመቱ
ጉልበቱን ቢያጠና
ብርሃን ፍለጋ
ስንኩአትን ስንተጋ
ብርሃኑም ጨለማ
የዋጠው ድቅድቅ
ይዞን ሊነጉድ ሻተው
ከዚያ ከአንጦሮጦስ
ከሲኦሉ ማቅ።
የብርሃኑን ውበት
የፀዳሉን ግርማ
የቅላጼውን ቅኝት
የስንኙን ዜማ
ከቶ ሳንረዳው
ይሉትን ሳንሰማ

ሊውጠን ቋዋመጠ

ደቅድቁ ጨለማ

*ሥዩም ደገፋ ጥቅምት 2000 ዓ.ም*

*ለሰሞነኛ*